በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሀምሃው

ከመንግሥቱ ገዳሙ

ሶ ማ ሌ ው

ከመ ንግሥቱ ገዳሙ

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ።

ይህች አነስተኛ መጽሐፍ የተዘጋጀችው ፤ ከእናት አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ባንድነት ለመዋሐድ ሲሉ በግፈኛው በሞቃዲሾ መሪዎች ለታረዱት ለሶማሌ ሕዝቦች መታሰቢያ እንዲሆን ተብሎ ነው ።

ፀሐዩ በጣም ያቃጥላል ። ሙቀቱ ትንፋሽ ያሳጥራል ። ልክ ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ሁለት የሱማሌ ወጣቶች አንድ በረንዳ አጠገብ ተቀምጠው ይከራከሩ ነበረ ። ከነሱ ትንሽ ራቅ ብሎ ወደሚገኘው የፈረሰ ግንብ አጠገብ አንድ ሽማግሌ ሰውዬ ተቀምጦ ትንፋሽ አጥሮት ይንሰፈሰፍ ነበረ ። ሰውነቱ ከመቁሰሉ የተነሣ ዝንቦች ወረውት ሲመዘምዙት እጆቹን አንቀሳቅሶ ለመከላከል ያቃተው ይመስላል ። እንደእውነቱ ከሆነ ሰውዬው በጣም ተጎሳቁሏል ። መልኩንና ሁኔታውን ሲመለከቱት ከእስር ቤት የተለቀቀ እስረኛ ሲመስል የዓይኖቹ መጎድጎድና አርቆ አስተዋይነቱ ከዚህ በፊት የኰራ ገበሬ እንደነበር ይነግርለታል ።

አዎን ሰውየው ብዙ ቤተሰብ የሚያስተዳድር እራሱን የቻለ ገበሬ ነበረ ። ከስምንት የሚበልጡ ልጆቹና ቤተሰቦቹ ወዴት እንዳሉ በደረሰበት ሥቃይ ምክንያት ከመዘንጋቱም በላይ እራሱም ያለበትን ሁኔታ አያውቀውም ። አእምሮው ደንዝዞ ሰውነቱ ተኰማትሮ በጣም ተጥለውልኋል ።

ወራቱ ሰኔ ሲሆን ከተማውም ሐርጌሻ ነው ። መንቀሳቀስና መላወስ ያቃተው ሰውዬ ለትንሽ ደቂቃ ያህል ሲተክዝ እንደቆየ ፤ አንድ ወፈር ያለ ሽጉጥ የታጠቀ አምሳለቃ ፖሊስ ከበስተጀርባው ከተፍ አለና ንቀት

ባዘለ ትእዛዝ « አሁንም ጥጋብህ አልበረደልህምን ? የመ
ንግሥታችንንስ ትእዛዝ ለምን አትፈጽምም ! መሣሪያ
ይዘህ ወደ ጠረፍ ሔደህ አትዋጋምን ? » ብሎ ደነፋበት

ሽማግሌው የተጥወለወለ ሰውነቱን በግድ አንቀሳ
ቅሶ ወደፖሊሱ የተዳከሙትን ዓይኖቹን ወርወር አደረ
ገና « እናንተ ነፃነት የምትሉት ፈሊጥ ምን እንደሆነ
ለማወቅ ግራ ገብቶኛል ። ነፃነት በምትሉት ፈሊጥ ፴
ዓመታት ሙሉ እጠቀምበት የነበረውን እርስቴን ከነከ
ብቶቼ ወሰዳችሁብኝ ። ነፃነት በምትሉት ከበሮ ከቤተ
ሰቦቼ ለያያችሁኝ ። አሁን ሚስቴ የት ናት ? ልጆቼስ
ወዴት ነው ያሉት ? እኔ ገበሬ ነኝ እንጂ ወታደር
አይደለሁም። እርግጥ ነው ፤ እውነተኛ ነፃነት ኖሮኝ አገሬን
ለመውረር ጠላት ቢመጣ ኖሮ ፤ ለሀገሬ ስል ደሜን
ከማፍሰስ አልቦዝንም ። አሁን እናንተ የምትሉት የጐረ
ቤትን አገር ድንበር ጣስ ነው ። ነፃነት ማለት በሰላም
እየኖሩ ጠግቦ እየበሉ የሀገርን ሁኔታ ማስከበር ነው
እንጂ እንዲያው ዝም ብሎ በመንጠራራት የሌላውን
ድንበር እንጣስ ማለት አይደለም ። ባህልንና ልምድን
ያልተመረኰዘ ነፃነት ጉም እንደመጨበጥ ያህል ነው ።
አሁን የቀረኝ መሞት ነውና ከሰላማዊ ሕዝብ ጋር ተዋ
ግቶ ከመሞት እናንተ በፈጠራችሁት ነፃነት በሚሉት
ዘዴ ተርቤ መሞትን ተዛምጃለሁና እባክህን በሰላም

መሞትን አትንፈገኝ » ብሎ ሽማግሌው ገሠጸው ።

ፖሊሱ በጣም ተናደደና ጠግቦ የበላው ሥጋ ተን
ሸራሸሮለት ስለነበረ ፤ እንዴ ሁለቱ አገሣና « ይህ እነጋ
ገርህ የግደሉኝ ልመና ነው ። እንደዚህ የመሰለውን ድፍ
ረት ተናግሮ በሕይወቱ የቆየ የለምና ተነሥ እንሒድ»
ብሎ እየገፈታተረው ወደአልታወቀ ቦታ ወሰደው ።

እነዚደ ሁለት የሶማሌ ጐረምሳዎች ክርክራቸውን
እንደቀጠሉ ናቸው ። አንደኛው እንግሊዝኛ በደንብ የተ
ማረ ሲሆን ፤ አንደኛው የኢጣሊያንኛ ቋንቋ ብቻ ነበር
የሚያውቀው ።

አንደኛው ወጣት ዓይኖቹን አፍጦ ጣቶቹን እያወ
ለበለበ « ከነፃነት ወዲህ በሀገራችን ውስጥ ከፍ ያለ
ፕሮብሌም ተፈጥሯል ። ቀለባችን የመስኩብ መሣሪያ
የአሜሪካን መኪና ሆነ ። ጥማችንን የምናረካበት ወሀ
የሞቃዲሾው ራዲዮ ጣቢያ ነው ። አልጋችን ጠመንጃ
ብርድልብሳችን መትረየስ ሆነ ። ነፃነታችን የመሪዎቻ
ችን ክርስ ሆኖ ቀረ ። ባልታረመ አንደበታችንና ባልተ
ለመደ ድርጊታችን ከጐረቤት መንግሥታቶች ጋር አቀ
ያይሞን ኑሮአችን መቅኖ አጣ ። የማይወዱትን ነገር
ማድረግና ያልተለመደ ሥራ መፈጸም ሞያችን ሆነ ።
እረ ለመሆኑ መጨረሻችን ምን ይመስልሃል ? » ሲል
ጠየቀው ።

ሁለተኛው ወጣት የጐረሰውን ጫት እዓላመጠ ፤ ሲጋራውን እንድ ሁለቴ ሳብ ላብ አድርጎ « እኔ » አለ እንዴ አገጣና « እኔ እንደሚመስለኝ ከሆነ ነገሩ በጣም አላማረኝም ። ባልታረመ ስድብና ባልተፈተነ ድርጊት ከጐረቤት ጋር በሰላም ለመኖር አንችልም ። በኃይል ተመክተን የሰውን ድንበር እንጣስ ፤ በስድብ የሌላውን አገር ይዞታ እናቃውስ ማለት የሕፃንነት ምኞት ነው ። ይህ ዓይነት ፕሮፓጋንድ ወደጥፋት እንጂ ወደልማት አይመራንም ። እንዲያው ለነገሩ ያለንበትን ቦታና ጊዜ ሳናውቅ ፤ በሌላው መንግሥት ባለሥልጣኖች ላይ የፈጠራ ስድብና በቅሌት የተቦካ ዘለፋ መሰንዘራችን ምን ለመሆን ነው ? እንደምታውቀው ሁሉ ፤ የአንድ አገር ነፃነት የሚመሠረተው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ልምድና ባህል ነው ። በጐሣ መነጣጠል የተነሣ ባህላችን ደፍርሶ እኛነታችንን አስፍቶናል ። ስለዚህ እኛ አሁን ባህል ወይንም ልምድ የምንለው ስድብና ዘለፋ ሆኖ ከቀረ ፤ በዓለም አካባቢ ውስጥ ምን ቦታና ስም ሊኖረን ይችላል ? » አለው ።

አንደኛው ጐረምሳ በሁለተኛው ወጣት አሳብ የተስማማ መሆኑን ለመግለጽ እራሱን ጉንበስ ቀና አደረገና «ሌላውን መንግሥት በመስደብ የተሻሻለ ሀገር እስከዛሬ ድረስ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም ። የአይ

በናንተ የተነሳ በምቾት የምናገኘውን ግጦሽ ለማግኘት አልቻልንም ሂዱ ወደውቅያኖስ ግቡ እያሉ እንስሶች የሞቃድሾ መሪዎችን ሲያባርሩ ።

ዶሎጂ ጦርነት የመንግሥትን ፖሊሲ እየተከተለ መሔድ
አለበት እንጂ ፤ በስሜት ስካር ተነሣሥቶ አንዳንድ ሰው
መስደብ ፤ ከጥቅሙ ይበልጥ ጉዳቱ ያይላል ። መሳስ እህ
ልን አይዘራም ። መሳስ የሃሳብ ማስራጫ መሣሪያ ነው
እንጂ ፤ ለተራበው እህል አይሆንም ። ትዝ ይልሃል ?
ከዚህ በፊት ሲጋራና ጫት በዱቤ ይሸጥልኝ የነበረው
ዋርሰማ አሁን እንደከለከለኝ ፤ በዚህ ረገድ ነፃነት ማለት
ጕሣ ለጕሣ እየተጋጨ ፍቅርንና ሰላምን አውድሞ በወ
ገን መሐል መተማመንና መዋደድን የሚያስቀር ምክ
ንያት ሊሆን ይገባዋልን ? መጀመሪያውኑ ባህልን ያልተ
ከተለ ልምድን የማያስታውስ ነፃነት በዕብዶች ዓለም
ውስጥ የሚገኝ ብቻ ነው ። የጐረቤት አገሮች የጥንቱን
ባህል ተመርኩዘው ባዲሱ ሥልጣኔ ሲገሰግሱ የኛ መሪ
ዎች ከጥንቱም ከአሁኑም ሳይሆኑ እንዳበደች ውሻ
ሁሉን የሚነካክሱበት ዘዴ ለነሱ ግላዊ ስሜት ማርኪያ
ሰበብ ሆነ እንጂ ፤ ለኛ ምንም አልጠቀመንም ። በመሪ
ዎቻችን ስሕተት ብዙ ፈተና ደርሶብናል ። እንደልብ
ወተት የሚሰጡን ከብቶች ሣር አጥተው ከማለቃቸው
የተነሣ በችጋር ተቈራምደናል ። እንደልብ ወደፈለግን
በት እየተዘዋወርን ሰምለሙን አገር አይተን መንፈሳ
ችን እንዳይረካ ፤ በፀሐይ ግንበኛነት በታጠረው አሸዋ
ታስረን እንሠቃያለን ። ሞት እንኳን ታዝቦን ዳር ቆሞ

መውሰዱን ጥሎ በሥቃያችን ቴያትር በሳቅ ይንሰቀሰ
ቃል » አለው ።

አብዶ የተባለው ሁለተኛው ወጣት በጣም እየተ
ከዘ « አዎን ስድብና ድንፋታ ለማንም ሲጠቅም አላየ
ንም ። ሙሶሎኒና ሂትለር ሞክረውት የመጨረሻ ግባ
ቸው አዘቅት ሆኖ ቀረ ። እነሱ እንኳን ቢሆኑ እራሳቸው
በሠሩት መሣሪያ ዓለምን ለመግዛት በጊዜአቸው ተው
ተረተሩ ። እኛ ምንድነን ? መሪዎቻችንስ ምን ለመሆን
ነው የሚጣጣሩት ? መጨረሻችን የጅብ ቁስል ሆኖ እን
ደሚቀር ምንም ጥርጥር የለውም ። ጅብ አንዴ የቆሰለ
እንደሆን ፤ ያንን ቁስሉን በመላስ የገዛ ሰውነቱን በልቶ
ይሞታል ። » ብሎ ንግግሩን ሳይደመድም ፤ አንድ ሐሰን
የሚባል ጓደኛቸው ስለመጣ ጨዋታቸውን አቋረጡና
ሰላምታ ተለዋወጡ ። ሐሰን ምንም እንኳን ጓደኛቸው
ቢሆንም በቅርብ ጊዜያት ከመስኮብ አገር ተምሮ የመጣ
የሞቃዲሾ ተወላጅ ነው ። ጓደኝነታቸው እንዲያው ለይ
ምሰል ተብሎ በምክንያት የተመሠረተ ነው እንጂ በአ
ሳብ በጣም የተራራቁ ናቸው ። ሐሰን ሁከትና ዓመፅ
ከመውደዱም በላይ ፤ የግዛት ማስፋትና የፈጠራ ስድብ
መንዛትን ይወዳል ። ለምን እንደሚሳደብ ፤ ለምን የሌላ
ውን መንግሥት ግዛት ገንጥሎ ለመውሰድ የሚያስመ
ኘውን የቀን ሕልም ምክንያቱን አያውቀውም ። ባጭሩ

ሐሰን የመሪዎቹ ቴፕሪኮርደር ነው ።

« እዚህ ተቀምጣችሁ በጊዜአችሁ ከመቀለድ ለምንድን ነው ጠመንጃ ይዛችሁ ወደ ጠረፍ ሔዳችሁ የማትሰለፉት ? ነፃነት እኮ በቀልድ አይገኝም ። መግደል ፤ ወሬ መንዛት ፤ የሌላውን መንግሥት መሪዎች መስደብ ይበልጡኑ ያጠነክረናል ። ስንሰድባቸው ይደናገጣሉ ስንገላቸው ይፈረጥጣሉ ። በዚያን ጊዜያት ግዛታቸውን እየቆራረስን እንወስድባቸውና እንጠቀምበታለን » ሲል ሐሰን ነገራቸው ።

አብዶ በሐሰን አነጋገር በጣም አዘነና እንዲህ አለው ። « ደም ሳይፈስ ፤ አጥንት ሳይከሰከስ የሰው ሕይወት ሳይረክስ በጐረቤት መንግሥታቶች ረዳትነት ያገኘነውን ነፃነት እንደተሰረቀ ገንዘብ ቈጥረነው ለምን እናባክነዋለን ? ኬንያ ከኮሎኒያሊስት ቀንበር ነፃ ለመውጣት ደሟን አፍስሳለች ። ኢትዮጵያም ምንም እንኳን ከሌላው አፍሪካ ሀገር ሁሉ ቀደምትነት ያለው ባህልና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ልምድ ፤ እንዲሁም መሠረት ያለው የነፃነት አቋም ሲኖራት ፤ እኛን ከኮሎኒያሊስቶች ጭቆና አድናን ነፃነታችንን እንድናገኝ የረዳችን አገር ስትሆን ፤ እንዴት ብንሳሳት ነው ግዛትሽን ገንጥለን እንውሰደው የምንለው ? ቂም በቀል በሌለው ወዳጅ ላይ ሁከትና ዘለፋ ማሰራጨት ምን ይጠቅማል ። የቀድሞ

አባባ እባክህን እራብኝ ሲለው በእህል ፋንታ ቦምብ ለሕፃኑ የሚሰጠው ጨካኙ የሞቃድሾ መሪ ።

ጌታዬ የነበረው ሲኞር አንቶኒዎ ማሪዎ ይተርተው የ
በረው ተረት አሁን ትዝ እያለኝ ሔደ ። ይኸውም «ደግና
ያደረገ ለውርንጫ ፤ ይቀበላል እርግጫ » የሚል ነበረ ።

« መበቀል ከፈለግን ከዚህ በፊት የጨቆኑንን ጣሊ
ያኖችንና እንግሊዞችን ነበረ ። ሀገራችን ውስጥ ገብተው
እኛንና መሬታችንን ወስደው ለብዙ ዓመታት እንደገ
ዙን ያህል ፤ አሁን እኛ በኢትዮጵያ ረዳትነት ባገኘነው
ነፃነት ፤ እንግሊዝንና ጣሊያንን እየዘለፍን መሬታችሁ
ቆርሳችሁ ስጡን ማለት ይቀናን ነበር እንጂ ፤ የጠላት
አማካሪዎችን በደል ረስተን እነሱ በሚመሩን መሠረት
ከጐረቤታችን ጋር መጣላት ባልተገባን ነበር ። አቅምን
ያለማወቅና ውለታቢስ መሆን ፤ እኛነታችንን ያረክሰ
ዋል ። ኢትዮጵያ እንኳን ለኛ ለሕፃን መንግሥት ይቅ
ርና ብዙ ሺህ ዓመታት ነፃነትና ሥልጣኔ ላላቸው ለቁ
ሣር መንግሥታቶች አገር ያልተበገረች ናት ። እስቲ
ማይጨውና አድዋን አስታውስ ! መሞት ከፈለግን መርዝ
መጠጣት ፤ መኖር ከፈለግን ኢትዮጵያና ኬንያ መጠ
ጋት ይበጀናል ። ስድ አደግ ሕፃን በአባቱ ላይ ምላሱን
ያወጣል ። እንዴት ያለ ልጅ ቢሆንና ምን ዓይነት ተፈ
ጥሮ ቢኖረው ነው የገዛ አባቱን ገድሎ የገዛ እናቱን
ለማግባት የሚጥር ? ጥንት የግሪክ ሚቲዮሎጂ ኤሮስ
የሚባል ወጣት አባቱን ገድሎ እናቱን ያገባው የገደ

ለው አባቱን ፤ ያገባት እናቱን መሆናቸውን ሳያውቅ እን
ደነበረ አስተዳደጉ ይመሰክራል ። ይሁን እንጂ ሚቲዮ
ሎጂ አዋልድ ወይንም ልብ ወለድ ታሪክ ነው እንጂ
እውነተኛ ታሪክ ሆኗል በማለት የሚታመንበት አይደ
ለም ። እዚህ ላይ አንድ ነገር ማስታወስ ሊያሻ ነው ።
የጥንት ሰዎች ልብ ወለድ ጽፈው በልብ ወለድነቱ
ታሪክ ዓለምን ሲያስደንቁ ፤ አሁን እኛ እንደእውነት
አስመስለን እተግባር ላይ እናውለው ብንል ዓለም ከግ
በዱም በላይ የሕልም ቅዠት ይመስለውና እንዲያል
ፈው ይገደዳል » እያለ ሲነግረው ፤ ሐሰን በጣም ተበሳ
ጭቶ ያዳምጠው ነበር ።

በመጨረሻው ሐሰን አላስችል ብሎት በአፉ ውስ
ጥ የሚያኝከውን ማስቲካ ተፋውና ፤ « እኔ እንደሚመ
ስለኝ ፤ አንተ የምትለው ከኢትዮጵያና ከኬንያ ግዛት
መሬት ቆርሰን መውሰዳችን ቀርቶ ከኢትዮጵያ እንቀላ
ቀል ነው ። አነጋገርህ ሌላ ምንም ምሥጢር የለውም
ይህ አነጋገርህ የሚገልጸው ጠመንጃ ይዘህ ለመዋጋት
መፍራትህን ነው እንጂ ሌላ ምሥጢር የለውም » አለ
ው በቁጣ ።

አብዶ ከተዝናናበት ስፍራ ተንቀሳቀሰና ፤ ዓይና
ቹን አፍጦ «አዎን» አለው ትኩር ብሎ እየተመለከ
ተው « አዎን እኛ ወዳጅ እንጂ ጠላት እንዲኖረን አን
ፈቅድም ። ኢትዮጵያ ማለት የሀገር ስም ነው እንጂ

የነገድ ስም አይደለም ። ሶማሌ ፤ ትግሬ ፤ ጐንደሬ ፤ ወላሞ ፤ ጐጃሜ ፤ ጋላ ፤ ጉራጌ ፤ እንዲሁም አያሌ ዘሮችና ነገዶች ባንድነት ተጣምረው ኢትዮጵያ ይባላሉ እነዚህ ነገዶች ልዩ ልዩ ቋንቋ ቢኖራቸውም ነፃነታቸውና ስማቸው ባህላቸውና የጋራ ብልጽግናቸው በአንድ መደብ ላይ የተመሠረተ ነው ። ሶማሌነቴን አውቄ ኢትዮጵያዊ ያለመሆኔን የተነገረኝ ፤ እናንተ አሁን ነፃነት በምትሉት የአርነት ተግባር ነው ። እኔ ዱሮ የማውቀው ሶማሌ ሲባል በኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ የምገኝ የአንድ ነገድ ሰው መሆኔ ነው ። ኢትዮጵያ የጋራ ስም መጠሪያችን ነው እንጂ የአንድ ነገድ ስም አይደለም ።

«በጣሊያ ግዛት ውስጥ ባጭሩ ፤ ሲሲሊ ፤ ካላብሪያ ፤ ካታንዛሮ ናፖሊ ፤ ፒዬሞንቴ ፤ ሚላኖ ፤ ፌሬንዜ ፤ ቶስካና ፤ የሚባሉ ነገዶች ሲኖሩ በጠቅላላው የሚታወቁት በኢጣሊያ ስም ነው እንጂ በየነገዳቸው አይደለም ። በአሜሪካንና እንዲሁም በየልዩ ልዩ አገሮች ቁጥራቸው ከመቶ የሚበልጥ ነገዶች ይገኛሉ ለምሳሌ እስኰትላንድ ፤ ዌልስ ፤ አይርላንድእና እንግላንድ ባንድ ዙፋን ሥር የሚተዳደሩ ዘሮች ናቸው ። ቋንቋቸውና ባህላቸው ትንሽ የተለያየ ቢሆንም ፤ እምነታቸው ፤ ነፃነታቸው ፤ አቋማቸውና ጥቅማቸው አንድ ነው ። የአሜሪካን ሕዝብ ብዛት በየነገዱ ሲደመር ከመቶ ስማንያ ሚሊዮን በላይ ነው ። ኢትዮጵያም ከ፳፫ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያለባት አገር መሆኑ ሲታወስ ፤ እኛ ትልቅ ሶማሊያ ለመባል የምንዳክረው ከሦስት ሚሊዮን የማይበልጥ ሕዝብ በሚገኝበት አገር ውስጥ ነው? ቆርሰን እንውሰድ የምንለውን የሌላውን አገር ግዛት ልናስተዳድር የምንችለው በየትኛው ባህላችንና ችሎታችን ነው ? ክብት ሰውን ያግዳል ወይንስ ሰው ክብትን ? የሰንበሌጥንና የወርካን ታሪክ እዚህ ላይ ማስታወስ ሊኖርብን ነው ።

« እርግጥ ነው » ። አለ አብዶ « እርግጥ ነው አንድ አገር በጠላት ሲወረር ፤ በቅኝ ግዛት ሥር ሲቀበር ፤ ነፃነቱን ለማግኘት ሲል ደሙን ያፈሳል ። አንዳንድ ጥጋበኛ መሪ ያለው መንግሥትም የሌላውን አገር ለመግዛት ታጥቆ ይነሣል ።

እኛ ጥጋበኛ ነን እንዳንል ፤ በረኃብ አለንጋ እንገረፋለን ። ኃይለኛ ነን እንዳንል ፤ በእህል ፋንታ ለዕርዳታ የሚሰጠንን መሣሪያ እንኳን ልንጠቀምበት ያልቻልን ነን ። ወጣቱ፡ ማረፊያ ፤ ሕፃኑ ማደጊያ ፤ ሽማግሌውና አሮጊቱ መጠጊያ እስኪያጡ ድረስ ማድረግ ዕብደት እንጂ የጤነኛ ሰው አሳብ አይደለም ። ስለዚህ እኔ የገለ ውለታዬን ግዛት ገንጥዬ ልውሰድ ከማለት ፤ እሱ ሥር

ሆኜ የሰው ልጅነቴን አቋም አስከብሬ በነፃነቴ እየተጠቀምኩ በተድላና በደስታ ለመኖር እፈቅዳለሁኝ ። መከራና ችግር በኀይል ሲመጣ መኀተር ይኖርብናል እንጂ እንዴት እኛው እራሳችን መከራ እንዲገጥመን እንሻብናለን ? እኔ እንደሌላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ፤ በሶማሌ ነገድነቴ እየኰራሁ ፤ በነፃነት ስሜ ኢትዮጵያዊ ተብዬ ለመኖር ቁርጥ አሳቤ ነው ። ይህንንም ስል ፤ ወደሸዋ ፤ ወደ ወሎ ፤ ወደ ሲዳሞ እሄዳለሁ ማለቴ አይደለም ። ኢትዮጵያዊነቴ እንዲረጋገጥልኝ የምፈቅደው እዚችው በተወለድኩበት የነገዶ ክፍሌ ነው ። አይ እዚህ ሆነህ ኢትዮጵያዊ እንድትሆን አንፈቅድልህም ብላችሁ ነፃነቴን ለመግፈፍ ከተነሣሣችሁ ፤ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያዋህደኝ ሌላ መሪ እስኪገኝ ድረስ ፤ የናንተን ግፍ ፊት ለፊት ቆሜ እከላከላለሁኝ ። ካልተቻለኝም ጊዜ እስኪገጥመኝ ድረስ ወደሸዋ ፤ ወደከፋ ተሰድጄ እኖራለሁ ። ይህ አይሆንም ብላችሁ በራሳችሁ ምኞት የምታስገድዱኝ ከሆነ ፤ ኢትዮጵያ ተብላ ጡት እያጠባችኝ ባሳደገችኝ እናቴ ላይ መሣሪያ ከመምዘዝ አስቀድሜ እራሴን እገድላለሁኝ » እያለ በምሮ ነገረው።

ሐሰን በዳሮት ነገድ ውስጥ የሚገኝ የመጀርቴን ጐሣ ተወላጅ ነው ። አብዶ ግን የኢሣቅ ጐሣ ሲሆን የእሬር ነገድ ነው ። የኢሣቅና የሐውያ ጐሣ የሚጠራ

መሠረቱ ጽልቅ የሆነውን የአፄ ፋሲልን ግንብ በገመድ ጠልፎ ለመጣል መሞከር ይህን የመሰለ አደጋ ያተርፋል።

በት የነገድ ስም እሪር ስለ ሆነ ፤ በመካከላቸው ያለመ
ግባባት በየጊዜው እየተፈጠረ እርስ በራሳቸው መተላ
ለቅን አላቋረጡም ።

ሐሰን በአብዶ እውነተኛ አነጋገር እንደመስማ
ማት ፋንታ ፤ የቀድሞ ቂጣውን ሳያለዝበው ፤ «እገሌ
ውለታ ሠራልኝ ብሎ ግዛቱን ቦጭቀን አንወስድም
ማለት ትልቅ ስሕተት ነው ። ይሉኝታና አገር ማስፋ
ፋት ጐን ለጐን አይሄዱም ። እኛ አሁን ያለብን ግዴ
ታ ፤ ሽማግሌ ፤ ሴትና ሕፃን ሳንል ሁሉም ባንድነት
ታጥቆ ጠረፍ እየጣሱ ሄደው መግደልና መሬት መን
ጠቅ ነው ። ይህ የመንግሥታችን ቁርጥ አሳብ መሆኑን
መዘንጋት አይገባችሁም ። ይህንን ዓላማ የተቃወ
ሙና ከኢትዮጵያ ጋር እንቀላቀላለን ብለው የተነሱት
ሁሉ በመትረየስ ተመታትረው አልቀዋል ። እናንተም
እንደሌሎቹ እልኸኛ ከሆናችሁ የሞት ጽዋ እንደሚደ
ርሳችሁ አትጠራጠሩ ። ዋና ዓላማችሁ መግደል ፤ መሳ
ደብና መሬት መቀማት ነው » አለው ።

አብዶ ከቀድሞው ይበልጥ ተገረመና « ነፃነት
የምትሉት አርነት ከመምጣቱ በፊት ወተት እንደልብ
እንጠጣ ነበረ ። ሥጋም በግፍ እናገኝ ነበረ ። ይኸ
ውም ያላንዳች ሥጋት ወደኢትዮጵያ ጠረፍ ከብቶቻች
ንን እያስገባን ግጦሽ እንዲያገኙ በማድረግ ነበር ።

አሁን ግን እናንተ በጫራችሁት የእሳት ነበልባል ከብ
ቶቻችን የሚበሉት ሣር አጥተው ከማለቃቸውም በላይ
እኛም በችጋር አለንጋ በመገረፍ ላይ ነን ። እኛ ማየት
ያለብን የሕዝቡን ጠቅላላ ችግር ነው እንጂ የመሪዎቻ
ችን ከርስ መሙላቱን ብቻ አይደለም ። እህል ፍለጋ
ስንቱ ወደ ኢትዮጵያ ተሰደደ ፤ ነፃነት በመምረጥ ስንቱ
የኢትዮጵያ ጥገኛ ለመሆን ተባረረ ፤ ከመሪዎቻችን
ጭቆና ለመዳን ሲል ስንቱ ደሙን አፈሰሰ ። በዚህ አስ
ተያየት በሶማሊያ አገር ውስጥ ትልቅ አናርኪስም ተፈ
ጠረ ማለት ነው ። አናርኪስም ሕግ ፤ ልምድ ፤ ስነ
ሥርዓትና ባህል የማይታወቅበት የአንድ አገር የአገዛዝ
ውጥንቅጥነት ነው ። የመሪዎቻችን ዴማጐግነት ለሕ
ዝቡ አንዳችም ጥቅም አይሰጥም ። ዴማጐጂ ለሕዝቡ
ተቆርቋሪ በመምሰል የግል ምኞትንና ጥቅምን ማዳበ
ሪያ የሆነ ልዩ ዘዴ ነው ። በአንድ እፍኝ ሩዝ ገበሬው
ንና ዘላኑን ሂድ ተጋደል ማለት ምን ይጠቅማል ?
መሬት የምናርስበት በሬአችን የጠመንጃ ቃታ ሆነ ።
የምናሰማራቸው ከብቶች የአሜሪካንና የመስኮብ መሣ
ሪያዎች ሆኑ ። መነሻ የሌለው ነገር መድረሻ አይገኝለ
ትም ።

«ለአዲሲቷ አፍሪካ መጥፎ ምሳሌ ሆንን ። ከኰ
ሎኒያሊስቶቹ እጅ ገና ከመውጣታችን ፤ እኛው እራሳ

ችን ኩሉኒ ለማድረግ ነፃ ያወጣንን መንግሥት ጥዋትና ማታ እንነዘንዘዋለን ። እስከመቼ ድረስ የቦምብ ቁጣና የመትረየስ ወሀ እየጠጣን እንቆያለን ። የመሪዎቻችን ልጆች በደስታ ይንደላቀቃሉ ። የእኛ ልጆችስ ወዬት ነው ያሉት ? አንተ ማየት ያለብህ በየሥርቻው ተጐሳቁለው የሚጨናበሱትን የወገኖችህን ሥቃይ ነው እንጂ የሞቃዲሾ ራዲዮና የመሪዎችህ ፕሮፓጋንድን አይደለም ። እስቲ አስብ ! » አለና በኃይል ደነፋበት።

በአብዶ አነጋገር ሐሰን ትንሽ ግራ ገባው ። የሞቃዲሾ ራዲዮ የሚናገረው ሌላ ነገር ነው ። መሪዎቹም የሚሰጡት ተስፋና ድንፋታ ሌላ ነገር ሆነበት ። የሐሰንን አሳብ እንዳይከተል በሞቃዲሾ ራዲዮ አማካኝነት አሳቡ ተወናጂብል ። ወኔውም ቀዝቅዞ በመኖር ግዴታ ያለበትን ሁኔታ ረስቶታል ። የአብዶ አነጋገር በመጨረሻ ሐሰንን ወደማሰብ ዝንባሌ ፤ መንፈሱ እንዲመራ አደረገው ። እሱነቱንም ለማወቅ በቂ ምክንያት ሆነለት ።

ሐሰን ትንሽ ከተከዘ በኋላ ፤ « አንተ የምትናገረው ነገር ሁሉ እውነት እየሆነብኝ ሄደ ። ይህ መሆኑን ሳላውቅ ራዲዮውና ጋዜጣው በሚነዛው ወሬ ተሳስቼ ወደ መጥፎ እምነት አዘንብዬ ነበር ። በኢትዮጵያና በኬንያ ላይ ብዙ ዘለፋ አስተጋባሁ ። ባደረግኩት ስሕተት ሁሉ አሁን የሕሊና ጸጸት ይሰማኝ ጀመር ።

ኧረ ለመሆኑ ፤ ከዚህ በፊት ላጠፋሁት ስሕተት ራሴን ምሬው ዳግመኛ እንዳልሳሳት ቁርጥ አሳብ ባደርግም ፤ ኢትዮጵያና ሕዝቡ አይበቀሉብኝምን ? » አለ በኀዘን

« አንተ ባታውቀው ነው እንጂ ኢትዮጵያ የነፃነት መጠሪያ ስም ነች ። ከሞቃዲሾው ግፍ ወደኢትዮጵያ እየተሰደዱ የሚኖሩት ሕዝቦች ቁጥራቸው በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ነው ። ኢትዮጵያ የሁላችንም እናት እንደመሆኗ መጠን ፤ ምሕረቷም በእናትነት ባሕርይ የተወሰነ ነው ። እሱዋ ፤ እኛ በማናውቀው ነገር ውስጥ ገብተን እንዳናልቅባት ነው እንጂ የምትደክመው ፤ ስድባችንና ሥራችንን የዝንብ ያህል አልተሰማትም ። የ፫ሺህ ዓመታት ዕድሜ ያላት አገር ከአራት ዓመት ዕድሜ ካለው ሕፃንዋ ጋር መታገል ያቃታት ይመስልሃልን ? የዲክቴተርና የሕፃን አኀር ዕድሜ የለውም ። የባቲስታ ፤ የሂትለር ፤ የሙሶሊኒ ፤ የናፖሌዎን ፣ የአሌክሳንደር ፤ የጃንክስካህን ፤ የሉዊስ አገዛዝ ወድቋል ። ለምን ተብሎ ሲጠየቅ መልሱ ቀላል ነው ።

«ዲክታተሮች ፤ ባህል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ልምድ ስለሌላቸው እንዶ ብቅ ይሉና ወዲያውኑ ድርግም ይላሉ ። የሚደለል ሕዝብ እንጂ በኃይል የሚገዛ ሕዝብ ከቶውንም የለም ። ኃይልና ድለላ ሁለቱም አንድ ዓይነት መሥመር ቢኖራቸውም ፤ አንዱ ካንደኛው

አይሻልም ። ሁለቱም ወዳቂዎች ናቸው ። የኢትዮጵያ
ሕዝብ ጥቅሙንና ጉዳቱን ያውቃል ። የማይበገር ጀግ
ንነት ፤ የማይረሳ ልምድ ፤ የማይለቀቅ ባህል አለው ።
ባህላቸውና ጀግንነታቸውን የሚያስጠብር ፤ ጨውነትንና
ብልህነት ከ፫ሺህ ዓመታት በላይ ከነበሩት ቅድመ አያ
ቶቹ የወረሰው ቋሚ ጥበብ ያለው መሪ አላቸው ። የኢ
ትዮጵያ ሕዝብ ባህሉን የሚያደፈርስበት መሪ አይቀበ
ልም ። ከዚህ በፊትም ባህልን ለማደፍረስ በስብከት
መሣሪያነት የተነሣ መሪ ነበራቸው ። ይህንንም የነገ
ረኝ አባቴ ነው ። መሪውን ሕዝቡ ስላልተቀበለው ፤
ከሥልጣን አወርዶታል ። እንደምንመለከተው የሶማ
ሊያ መሪዎች የሚፈጽሙት ተግባር ሁሉ ከሶማሊያ
ሕዝብ ፍላጎት ውጭ ነው ። ሕዝቡ ዓይኖቹ ካልታ
ወሩ ፤ ጆሮቹ ካልደነቆሩ በስተቀር ይህን የመሰለ ተግ
ባርና ድርጊት ዝም ብሎ ማለፍ የለበትም » አለው።

ሐሰን ነገሩ እየገባው ሄደ ። መደንፋቱንና ሞባረ
ቁን ረሳው ። አንገቱን እያቀረቀረ መተከዙን ቀጠለ ።
ነገር ግን አንድ ነገር ቅር ብሎታል ። ለመጠየቅ እየ
ፈለገ ይተወዋል ። በመጨረሻ አላስችል ብሎት በጥ
ሞና አንደበት « ኢትዮጵያ ከአምስቱ ዓመታት የፋሺ
ስት ወረራ በስተቀር ከ፫ሺህ ዓመታት በላይ ሥልጣኔና
ነፃነት ያላት አገር ናት ትባላለች ። ስለዚህ ከሌላው

አገር ሁሉ የቀደመ ነፃነትና ሥልጣኔ ካላት ለምንድ
ነው አሁን ወደኋላ ቀርታለች የሚባለው ።

አብዶ በሐሰን አወላዋይነትና ሞኝነት ተደንቆ
እየሳቀ እንዲህ አለው ። « የዛሬ ፫ሺህ ዓመታት ያል
ኖረ መንግሥትና ሕዝብ አይገኝም ። ኢትዮጵያ ብቻ
ዋን አልኖረችም ። እስካለፈው ፴ ዓመታት ድረስ
ሁሉም የአፍሪካ ሕዝቦች የሦስት ሺህ ዓመታትና ከዚ
ያም የበለጠ ዕድሜ ነበራቸው ። ከሰባ ዓመታት ወዲህ
አንዳንድ የአፍሪካ ጥቅም ፈላጊ መሪዎች ለኰሎኒያሊ
ስቶች በር ስለከፈቱላቸው ፤ ለጊዜው ነፃነታቸውን እን
ዲያጡ ሆኑ ።

ሌሎቹ በራቸውን ከፍተው ለኰሎኒያሊስቶች መግ
ቢያ ሲሰጡ ፤ ኢትዮጵያ ፊት ስለነሳቻቸው አልተደፈ
ረችም ። ይኸውም በመሪዋ ኃይልና ጥበብ መሆኑን
መገንዘብ ያስፈልግሃል። ሥልጣኔ ያልከው ግን ምን እንደ
ሆነ አልገባኝም ። በግሪክ ሥልጣኔ የአክሮፖሊስን ታሪክ
በሮም ሥልጣኔ ፤ የኰሌሲዩምን ፤ በኢትዮጵያ ሥል
ጣኔ ላሊበላእና አክሱም በመባል የታወቁ ህንፃዎች
ናቸው ። በሮም ሥልጣኔ በኰሊሲዩም ውስጥ ሰውና
ሰውን እያጋደሉ ፤ በመጨረሻው ክርስቲያኖችን በአን
በሳና በነብር ያስበሉ ነበረ ። በግሪክ ሥልጣኔ አክሮፖ
ሊስ የመወያያ ና የፖለቲካ ሐሳብ መግለጫም ከመሆ

እኛ ያንተ ስብከት አይጠቅመንም ይዘህ መሣሪያህን ብቻህን አቅራራ እያሉ ደጉ የሶማሊያ ሕዝብ ከሞቃድሾ መሪ ሲሸሹ ።

ኑም በላይ ፤ ዜውስ ሊተባለው ጣኦት መስገጃ ቤታ ሲሆን ፤ በኢትዮጵያ ሥልጣኔ አክሱምና ላሊበላ የመንፈሳዊና የባህል ጠንካራነትን የሚገልጹ አቋሞች ናቸው ። የግሪክ ሥልጣኔ ወድቋል ። የዛሬ ፪፻ ዓመታት የነበረው የሮም ሥልጣኔ ወድቋል ። አወዳደቁም በመሪዎቻቸው ዲክታተርነት መሆኑን ታሪክ ይነግረናል ። የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ግን አልወደቀም ። ይህ አንደኛው ዓይነት ሥልጣኔ ተብሎ የሚጠራው ነው ።

ሁለተኛው ሥልጣኔ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ነው ። ሌሎች የአፍሪካ አገሮች በቅኝ ግዛት አስተዳደር ውስጥ በነበሩበት ወቅት ፤ ኢትዮጵያ እንደቀለበት ድንበሯ ቱከቦ የውጭ መተንፈሻ ያልነበራት አገር ነበረች ። ይሁን እንጂ ፤ ነፃነቷን ተደግፋ የውስጧን ሥልጣኔ ያላቋረጠች ናት ። በሯን አስከፍታ ወደፈለገችበት እንዳትሄድ በግፍ የተወረሩት የአፍሪካ አገሮችን ነፃ ማውጣት ይኖርባታል ። ይሁን እንጂ እነሱን ለመጋተር ኃይል አልነበራትም ። የሞከረችበትም ጊዜ ይኖር ይሆናል ። ይህን ሊያውቅ የሚችል ኰሎኒያሊስቱ ነው እንጂ ተገዢው አይደለም ። ሥልጣኔ በትልቅ በርሜል ዶኬ መቀቀል አይደለም ። በትንሽ ድስት የዶሮ ወጥ መሥራት ነው ። የአንዱ አገር ሥልጣኔ ብዙ ቤት መሥራት ሲሆን ፤ ያንደኛው አገር ሥልጣኔ ባህሉን

ማዳበር ነው ። ኢትዮጵያ ፳ እርምጃ ልትሄድ በምትነሣበት ሰዓት ፴ እርምጃ ወደኋላ የሚጐትቷት ምክንያቶች ነበሩ ። እነሱም እንደቀለበት የከበቧት ኰሎኒያሊስቶች ነበሩ ። » እያለ አብዶ አስረዳው ።

ሐሰን ጅግና በመምሰል ዓይኑን ያፈጥ የነበረው የርጎራሒ ጸጸት ናላውን አዞረውና እንደ ሕፃን ልጅ ያለቅስ ጀመረ ። መፈጠሩንም ጠላ ። ከዚህ በፊት እሱ የተማረው መጋደልና መሳደብ ነው እንጂ ፤ እናትና አባቱ ወዴት እንዳሉ አያውቅም ። ጉዱ እዚህ ላይ ነው ። ሺንገላና ስብከት እንዴት ፤ ነፃነትን ወላጅ እናትንና አባትን ያስረሳል ። የጥንት የሮማን ቄሣሮች ፤ ሰውና ሰውን በማጋደል ይደሰቱ የነበረው ሁኔታ ሁሉ ትዝ አለው ። የተሰጠው ጠመንጃና ሽጉጥ ፤ መሪዎቹ እንዲደሰቱ እንዲጋደልበት መሆኑን አወቀው ።

ሐሰን ትንሽ አሰበና ፤ « አሁን ምን ይበጀኛል ትላለህ ? » ሲል አብዶን ጠየቀው ።

አብዶም ሲመልስ ፤ « ነፃነት ማለት ኢትዮጵያ ነውና ፤ ኢትዮጵያዊነታችንን እናጠንክር ። አይ አይሆንም በማንም መደዶ እንመራለን ካልክ ፤ ሥጋህ ለጅቢራ ፤ ነፍስህ ለሰይጣን ነው የሚሆነው ። አሜሪካን ትልቅ አገርና የሀብታም አካባቢ መሆንዋ በነገድ አይደለም ። ጣሊያን ፤ እንግሊዝ ፤ ፈረንሣይ ፤ ጀርመን ፤

እሑድ ቤተ ክርስቲያን አርብ መስጊድ መሄድ ብቻ ሣይሆን የሞቃድሾ መሪ የተወሳሰበና የተደነጋገረ ባሕሪ ያለው መሆኑን በዚህ ሥዕል ለመረዳት ይቻላል ።

አይሁዲና አፍሪካዊ ሆነው ባንድነት ተቀላቅለው በኅ
ብረት በመራመድ ነው ። አንድ ነገድ ለሌላው ኑሮ
ምክንያት ይሆናል እንጂ ለራሱ አይጠቀመውም ። ስለ
ዚህ አሮጊቷና ሽማግሌው መኖሪያ እንዳያጡ ፤ ሕፃኑና
ወጣቱ መድረሻ እንዲያጣ የትልቅነትን በሽታ ወደኋላ
ጥለን ። የአጭበርባሪዎችን ስብከት ዘለን ከብቶቻች
ን ሣር እንዲግጡ ፤ እኛም በነፃነታችን ኰርተን በልተ
ንና ጠጥተን እንድናድር ፤ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል
ይበጀናል ። የተፈጠርነው ለመደሰት እንጂ ለመውቃ
የት አይደለም » አለ ።

ብዙ ሲያወሩ እንደመቆየታቸው ያህል ፤ ሰዓቱም
እያለፈ ሄደ ። አብዱ ለሐሰን ተገቢውን መልስ ሰጥ
ቶት ሐሰንም በአሳቡ ስለተስማማ ከፍ ያለ ደስታ ተሰ
ማው ። ምክንያቱም የዚያን ዕለት ተገናኝተው ይህን
የመሰለ ምክር ባይሰጠው ኖሮ ፤ በተሰበከው ወሬ ስሜ
ቱ ጋይቶ በያዘው መሣሪያ ሳይጠቀምበት የጅቢራ
እራት ይሆን ነበረ ። በሐርጌሳ ውስጥ ያሉት ሕዝቦች
በሞቃዲሾው ስብከት ሲሞኙ መከረማቸውን አውቀው
እኩሉ የነፃነት ያለህ እያለ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት በጥ
ገኝነት ሲገባ ፤ እኩሉ በወንበዴዎች መሪነት የተወለ
ድኩበትን ክፍለ አገር ለቅቄ አልሄድም በማለት
ጨለማ ለብሶ ደሙን ያፈሳል ።

እህልና ወሀ በሌለበት አገር ውስጥ የሱማሌ መሪ

ዎች የሰውን ሥጋ እየተመገቡ ደሙን እየጠጡ ለመ
ኖር የሚፈቅዱበት ምክንያት ለብዙ መንግሥታቶች እስ
ካሁን ድረስ ግራ ገብቶአቸዋል ። ስለነፃነትና ስለኢት
ዮጵያ ደግነት የተላለፈው ወሬ ፤ በሕዝቡ ጆሮ እየተሰ
ራጨ ሄደና በመጨረሻው የሶማሊያው ጠቅላይ ሚኒስ
ትር ወደ ኢትዮጵያ ለመሔድ ሲያስብ ስለተገኘ በኃይል
ታስሮ እንዲሠራ ተደርጓል ። በዚህ አስተያየት የሶማ
ሊያ መንግሥት የሚገዛው ባልታወቀ ወንበዴዎች እጅ
መሆኑን ይመሰክራል ።

ትንሽ ካሰበ በኋላ አብዶ እንደሚከተለው አሳብ
ሰጠ ። «እኛ እዚህ ሆነን የምንናገረው ነገር ሁሉ ነፃነ
ትና ምግብ አይሆነንም ። ካልበላን ለመኖር እንደማን
ችል የታወቀ ነው ። የሶማሌ ነገድ ነፃነቱን አውቆ
ኢትዮጵያዊ መሆኑን እስኪያውቀው ድረስ ወደኢትዮ
ጵያ መሔድ ነው ። ጥዋትና ማታ እንደምንመለከተው
በግጭት ቆስለው ለሕክምና የሚመጡትን ሰዎች የሶማ
ሊያ መንግሥት መድኃኒት እንደመስጠት ፋንታ ባንድ
ቦታ ቆልሎ በመትረየስ ከገደላችው በኋላ ፤ በቤንዚን
ያቃጥሏቸዋል ። ይህ አድራጎት ዕብድ ሆኖ በዕብደት
የሚፈጸም ተግባር ስለሆነ ፤ ለሰው የማይነገር ነው ።
እንደነገርኩህ ሁሉ አሳቤን የተቀበልከው ይመስልሃል።
ስለዚህ አንተ ምን ታስባለህ ? » ሲል ጠየቀው ።

« የኔ አሳብ የሶማሌ ነገድ ሆኜ ኢትዮጵያዊነቴ ታውቆ ነፃነቴን እስካውቅ ድረስ ወደኢትዮጵያ ግዛት በጥገኝነት እንድኖር አሁኑኑ መሔድ አለብኝ» አለና ለመ ጀመሪያ ጊዜ ትንፋሹን ተነፈሰ ።

የቀኑ ሙቀት በርዶ የምሽቱ ነፋስ አሸዋውን እያ ቅመዘመዘ ሲሔድ ፤ እየተገደዱ ለመጋደል የሚነዱ ሰዎች ቁጥር ከቀድሞው ይበልጥ መጠኑ ያነሰ ነበር ።